# ለሞት የቀረበ
## ክፍል ሦስት - የመጨረሻው ክፍል

ከበልጅግ አሊ

፩

አሁንም መስኮቱ ጋ እንደቆምኩ ነው ፣ ቀኑ እየገፋ ቢሄድም የጨፈገገው ሰማይ መሻሻልን አላሳየም ። ፀሐይ ጉልበቷ ዝሎ ፣ ሙቀቷ አልቆ ፣ ውሃ ያዘለው ደመና ሙሉ በሙሉ ሊሸፍናት ሲታገላት ጎስቋላ መስላ ነው የምትታየው። በመስኮቱ ወደ ውጭ ስመለከት ቀለብ ለመግዛት ከሚጣደፉ ሰዎች በስተቀር ይህንን ጨፍጋጋ ቀን ደፍሮ ለሸርሸር ወይም እንደተለመደው ውሻ አስከትለው የሚሄዱ አሮጊቶች እንኳን አይታዩም።

ኮምፒውተሩን ስላልዘጋሁት ሴትየዋ አሁንም ታጓራለች ። "ቀይ ሽብር የነጭ ሽብር ውጤት ነው" በማለት ትለፈልፋለች ። "ነጭ ሽብር" ስትል ምን ማለቷ እንደሆነ አልገባኝም። የደርግ ፕሮፖጋንዳ ትቶት የሄደው ቃል መሆኑን ብቻ ነው የምረዳው። ቀይ ሽብር በኢሕአፓ አባላት ላይ ብቻ የተደረገ እንዳልነበረ የታወቀ ነው ። ቀይ ሽብር እኔ እንኳ እስከማውቀው በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ላይ የታወጀ ሽብር ነበር። ቀይ ሽብር አረመኔዎች ሕዝቡን ሰጥ ለጥ አድርገው ለመግዛት እንደ መሣሪያ የተጠቀሙበት የግድያ ሽብር ነበር። ቀይ ሽብር "ለነጭ ሽብር" የተደረገ መልስ ነው የሚሉ የቀድሞ ጥፋታቸውን ለማካካስ ይሆን ? ይህንን ምክንያት በማቅረባቸው ሊደርስባቸው ከሚችለው ጭንቀት መሸሽ ይችላሉ?

ዶስቶየቭስኪ (Crime and Punshiment) በሚለው መጽሐፉ የፈጠረው ገፀ - ባሕርይ ራስኮልኒኮቭ አራጣ አበዳሪዋንና እህቷን በመግደሉ ምንም እንኳ ነፍስ ማጥፋቱን የሚያረጋግጥ መረጃ ተገኝቶበት ፣ በፖሊስ ባያስጠይቀውም ሌሊት በዕንቅልፉ ፣ ቀን በሃሳቡ እየመጣ ይረብሸው ነበር ።ከዚህ አሰጨናቂ ከሆነው ቅዠቱ ለመውጣት የገደላት አራጣ አበዳሪ ክፉ ነበረች ብሎ መወንጀሉና ይህንን አምኖ መቀመጡ ብቻ ሊረዳው አልቻለም ።ለሠራው ጥፋት ማካካሻ መፈለጉ ይበልጥ ጭንቀት ውስጥ ከተተው እንጂ ለሕይወቱ እረፍት አልሰጠውም ። ከዛ የቅዠት ሕይወት ውስጥ ለመውጣት አንድ መንገድ ብቻ ነበረው ።ጥፋቱን አምኖ እውነቱን መናዘዝ።ለፖሊስ ተናግሮ በሳይቤሪያ ቅጣቱን እንዲቀበል ከተወሰነበት በኋላ ነበር በሕይወቱ ድንቅ የሆነውን እረፍት ያገኘው ። በየጊዜው እየተመላለሰ ሲያስጨንቀው የነበረው የገደላቸው ሴቶች ፊት ከኅሊናው የጠፋው። ይህንን ኑዛዜውን እንዲፈፅም የረዳችው ሶኒያ በወንጀል የተጨማለቀ የድሎት ወይም ነፃነት የጎደለው ኑሮ ከመኖር ፣ በኑዛዜ የነፃ ትንሣዔን በመመኘት ከእሱ ጋር አብራ ወደ ሳይቤሪያ በመጓዝ የስቃይና የደስታውን ኑሮ ተካፍላዋለች ።

ምንአልባት በሃገራችን በቀይ ሽብር ወቅት በሰው ደም የተበከሉ ግለሰቦች ለጥፋታቸው ማካካሻ ለማግኘት የሚያደርጉትን ሙከራ አቁመው ወንጀላቸውን ቢናዘዙ ወደፊት ለሚጠብቃቸው እውነትንና ፍትሕን ያንፀባረቀ የነፃነት ትንሣዔ፣ ሶኒያ ለራስኮልኒኮቭ እንዳደረገችው በድጋፍ እናጅባቸዋለን እንጂ ዛሬውኑ በሞት ካልተቀጡ ብለን ፣ ወይም ደግሞ በየመንገዱ እየተሳለቅንባቸው ሕይወታቸውን የቁም ገሃነም እሳት አናደርገውም።

የደርግ ካድሬዎች አሁን እንኳን መለስ ብለው ሲያዩት በንፁሐን ደም እንደተለወሱ ማስተዋል እንዴት ይሣናቸዋል? እንዴትስ እውነተኛ የሕሊና ወቀሳ ያጣቸዋል? ከሠላሳ ዓመት በኋላ ቀይ ሽብርን ደግፎ የሚጮህ፣ የሚናገር ፣ የሚጽፍ ፣ ይኖራል ብሎ ለማመን ያዳግታል ። ይህንን ዓይነት አሳፋሪ ተግባር የሚፈፅሙ ግለሰቦች ተሳክቶላቸው ወደ ሥልጣን ቢመለሱ ለሚቀጥለው ትውልድ ሊያወርሱ የሚፈልጉት ይህንን አስከፊ ዘመን መመለስ መሆኑን ያሁኑ ሁኔታቸው ጎልቶ ያሳያል።ዛሬ በየውጭ ሃገር ከተሞች ውስጥ ተሰግስገው ፣ የቀድሞ ታሪካቸውን ደብቀው ፣ ዘመኑ በፈጠረላቸው የዘር ድርጅቶች ተሰግስገው ፣ ወይም ከጀርባ ሆነው፣ ያንን ትውልድ ማውገዙ ለሁለተኛ ግዜ ፍርድን እያጓደሉ በሞቱት ወገኖች ላይም እየቀለዱ እንደሆነ ነው የሚያሳየው ። ይህ አመለካከትም ይበልጥ ወደ ጥፋት መንገድ እየመራቸው ነው ብዬ አምናለሁ። በሃገራችንም ላይ እውነተኛ ፍርድ እንዳይሰፍን ዕንቅፋት ሆኗል።

ሃሳቤ እንደገና ያለ ጥፋቱ በሞት ወደ ተቀጣው የቴክሳሱ የደብዳቤ ጓደኛዬ ሄደ ። አንድ ደብዳቤውን አውጥቼ ማንበብ ጀመርኩ። ደብዳቤው ሞት ተፈርዶበት ወደ ሌላ እስር ቤት በተቀየረ ጊዜ የገጠመውን የሚተርክ ነው ። ........

እስር ቤት የገባ ሁሉ ጥሩም ይሁን መጥፎ የመጀመሪያ ቀን ታሪክ አለው ።እኔም ከሌሎቹም የተለየ ባይሆንም የደረሰብኝን ላካፍልህ። ምን አልባት ከዚህ ደብዳቤዬ ብዙ ልትማርበት ትችላለህ።

___ ወደ ምሳ ሰዓት አካባቢ ነው የእስር ቤቱን ፍተሻ ሥነ ሥርዓት ጨርሼ ኤሊስ ኸንትስቪል ውስጥ ኤሊስ ዩኒት በሚባል እስር ቤት (Ellis Unit in Huntsville (H – 20) በሚባል ጠባብ ክፍል ውስጥ ተመደብኩ ።በዛች ጠባብ ክፍል ውስጥ አንድ ፍራሽ ፣ አንድ ትራስ ፣ ሁለት አንሶላ፣አንድ ብርድልብስና የሽንት ቤት ወረቀት አለ ። ግን ያንን ሁሉ ለማየት ምንም የተሰባሰበ ልቦና አልነበረኝም ። እዛች ክፍል ውስጥ ተቀምጬ ሙሉ በሙሉ በሃሳብ ውቅያኖስ ውስጥ ጠፍቼ ነበር።ልዩ ልዩ መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች በአዕምሮዬ ውስጥ ተጉላሉ።የሃሳብ ሱናሜ እረፍት ነሳኝ ።

እኔ እዚህኛው እስር ቤት በመጣሁበት ወቅት ሞት የተፈረደባቸው እስረኞች እንዲሠሩ ይፈቀድላቸው ነበርና እኔ ክፍል አካባቢ የሚያስጠላ ትልቅ ቦት ጫማ አድርጎ የሚጠርግ አንድ እስረኛ ቆሞ ነበር ። የእስረኛው ስም ናፖሊዮን ነበር ። የናፖሊዮን ሥራ ውጭውን ማጽዳትና ለእስረኛው ምግብ ማስተናገድ ነበር። ወደ እኔ ክፍል ተጠግቶ ፍርግርግ በሆኑት ብረቶቹ መሃል እየተመለከተ አዲስ መሆኔን ጠየቀኝ። እኔም ገና መምጣቴ መሆኑንና ስሜን ነገርኩት ። ስሜን በመንገሬ ምንም ችግር እንደማይገጥመኝ በመተማመን ነበር የነገርኩት ። ወደ ማህል ሄዶ ሁሉንም እስረኞች የሚመለከትበት ቦታ ላይ ቆሞ “ እዚህ አዲስ የመጣ ሰው አለ። ስሙም ሊውስ ይባላል“። ብሎ ጮኾ መናገር ጀመረ።ስሜን በመንገሬ የተሳሳትኩ መሆኑን ወዲያው ገባኝ።ስለዚህ እስር ቤት ውጭ ሆኜ የሰማሁትን ረስቼ ስሜን መናገሬ እኔን ለሚያጠቁ በቀጥታ የመምጣቴን መልዕክት እንዳስተላለፍኩላቸው ታወቀኝ ። በግል እዚህ እስር ቤት እኔን ለማጥቃት የሚፈልግ አለ ብዬ አላምንም። ግን የአሁኑ የናፖሊዮን ጥሪ ጓዶኞቹን ሁሉን መሰብሰቡ እንደሆን ገባኝ ። ጠቅላላው እስረኛ መጥቶ በፊልም እንደተመለከትኩት የሚያሰቃዩኝ መሰለኝ ። ልቤ ተጨነቀ ።እዚህ የተሰበሰቡት “ነፍሰ ገዳዮች“ ለእኔም እንደማይራሩ አሰበኩ።

ከእራት በኋላ ናፖሊዮን እንደገና መጥረጉን ጀመረ ። እኔም ሰዓቱ መድረሱ ምልክት ስለመሰለኝ ለመጨረሻው ሰዓት ተዘጋጀሁ ። ናፖሊዮን ወደ እኔ ክፍል ተጠግቶ በኪስ ወረቀት ውስጥ ያለ ዕቃ አቀብሎኝ ሄደ ። ምንድነው ? ብዬ ጠየቅሁት ። ተመልከተው ብሎኝ በፍጥነት ወደ ሥራው ተመለሰ። በውስጡ ምን እንዳለ ማሰብ አቃተኝ ። በጣም መጥፎ ነገር እንዳለ ግን አልተጠራጠርኩም ። ከመክፈቴ በፊት ብዙ ነገር ታሰበኝ ። ከተቆረጠ የሰውነት አካል እስከ አፀያፊ ነገሮች ሁሉ አሰብኩ። በአንድ ጊዜ አዕምሮዬን አወኩት።ወረቀቱን ልክፈተው አልክፈተው ብዬ ከራሴ ጋር ሙግት ገጠምኩ ። ወረቀቱን በጥንቃቄ ስከፍተው “ነፍስ ገዳይ“ ተብለው ከታሰሩ ሰዎች በፍፁም የማልጠብቀው ሆኖ አገኘሁት።

በኪስ ወረቀቱ ውስጥ የነበረው እስር ቤት ውስጥ የሚጠቅመኝንና የሚያስፈልጉኝ ዕቃዎች ነበሩበት። የደብዳቤ ቴምብር ፣ ፖስታ ከነወረቀት ፣ ጭቃ ቀለም ( እስክሪፕቶ ) ሳሙና ፣ ሻንፖ ፣ የጥርስ ሳሙና ፣ የጥርስ ቡርሽ ፣ እና ሌሎች ነገሮችም ። እራሴን በጣም ታዘብኩት ። እኔም ለካ እንደሌላው ነፍስ ገድለዋል ተብለው የተያዙትን በሞላ እንደጭራቅ ነበር የማያቸው ። በዚህ እስር ቤት በፍትህ ጉድለት የታሰሩ እንዳሉ እንኳ ለማሰብ ተሳነኝ።

ናፖሊዮንን ጠርቼ ከማን እንደተላከልኝ ጠይቅሁት ። ሁሉም እስረኛ ያለውን አዋጥተው የላኩልኝ መሆኑን ነገረኝ ። እነዚህ ዕቃዎች ለማግኘት ጊዜ ስለሚወስድብህ ነው ብሎ አስረዳኝ ። ለመክፈል እንደምፈልግና ማን ምን እንዳዋጣ ለማወቅ ስለፈለግሁ እንዲነገርኝ ደግሜ ጠየቅሁት። እሱ ግን የዚህ እስር ቤት ህግ እንደሱ አይደለም ብሎ አስረዳኝ። በሚቀጥለው ሌላ እስረኛ ሲመጣ አንተም ማዋጣት እንዳለብህ እንዳትረሳ። በዛም መንገድ ነው ዕዳህን የምትከፍለው ብሎ ሕጉን ነገረኝ።እያንዳንዱን ዕቃ እያወጣሁ መመልከት ጀመርኩ ።

በነጻው ዓለም በኖርኩበት ግዜያት ስንት ጥሩ ሰዎች እንደገጠሙኝ አሰብኩ ። እኔ እራሴ መንገድ ላይ ተቀምጠው በወረቀት ላይ ፅፈው እርዳታ ለሚጠይቁ ሰዎች ምንም ሳላደርግላቸው

ያለፍኩባቸውን ጊዜ አስታወስኩ ። ለእነዚህ ሰዎች ለአንድ ጊዜ እንኳ እርዳታ ባደርግላቸው ኖሮ ምን ያህል እንደሚደሰቱ የገባኝ አሁን እኔ ምን ያህል እንደተደሰትኩ ሳየው ነው ።

በዚያ በኪስ ወረቀት ውስጥ ያለው የሰው ልጅ ለሌላው የሰው ልጅ ሊያሳየው የሚገባ ፍቅር ፣ ደግነት ነው ፣ ሰብዓዊነት ነው ። ይህንን ፍቅር ፣ ሰብአዊነት ፣ አሳቢነት ፣ ደግነት በነጻው አለም ውስጥ እንኳ ለማግኘት የሚከብድ ነው። በዚህ መጥፎ የተባሉ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ይህንን የመሰለ ደግነት ለማያውቁት ሰው ለማድረግ ወደ ኋላ የማይሉ ግለሰቦችን ለማግኘት መቻሌ በነፃው አለም ላይ በነበርኩበት ጊዜ ማድረግ እችለው የነበረውን ሁሉ ጉልህ አድርጎ አሳየኝ ። እስረኞቹ ይህንንም ያደረጉልኝ ክፍያን ወይም ማድረጋቸው እንዲታወቅላቸው አይደለም። ማድረግ የሚገባቸው ሳይጠየቁ ያደረጉት ለምስጋናም ወይም ብድር ለማቆየትም አልነበረም ።

በሕብረተሰቡ ውስጥ ሕግ አስከባሪ ተብለው በመንግሥት ተወክለው ፍርድም ለመወሰን የተመረጡ ሰዎች ሊያደርጉልኝ የቻሉት አደረግሁት ለተባለው ወንጀል መረጃ ሳይገኝ በሞት እንድቀጣ መስማማትን ብቻ ነበር ። ግን ገንዘብ ኖሮኝ ጥሩ ጠበቃ ቢኖረኝ ኖሮ ደግሞ ነፃ እሆን ነበር ። <u>**ፍርድ በገንዘብ አቅም ሲወሰን ፍትሕ ይጓደላል**</u> ። በዚያች ክፍል ውስጥ ተቀምጬ ሞት የፈረዱብኝን አስራ ሁለት ሰዎች አሰብኩ። <u>***ማን ይሙት ማን ይዳን ብለው መወሰን የሚችሉ የእግዜርን የሚያክል ሃላፊነት ከቴክስስ አስተዳደር የተሰጣቸው ነበሩ።ግን የፈጣሪን ያህል ሥልጣን እንጂ የፈጣሪን ያህል ዕውቀት፣ ንፁህና ወንጀለኛውን ለመለየት ችሎታ አልነበራቸውም ።***</u>

እነዚህ ሰዎች ከሕብረተሰቡ የተሰጣቸውን ሃላፊነት ለመወጣት መሞከራቸው መሆኑን አልጠራጠርም።በእነሱም ላይ አልፈርድባቸውም። ከዳኛውና ከአቃቤ ሕጉ የተነገራቸውን ሕዝባዊ ሃላፊነታቸውን መወጣታቸውም ይሆናል። እኔ በበኩሌ የነፍስ ማጥፋት ጉዳይ ሕዝባዊ ሃላፊነት ነው ብዬ አላምንም። የእግዜርን ያህል ዕውቀት የሌላቸው ሰዎች የእግዜርን ያህል ሥልጣን አይገባቸውም ። እዚህ ሰሜን አሜሪካ ውስጥ ብዙ ሰዎች የሞት ፍርድ ከተፈፀመባቸው በኋላ ከወንጀሉ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው ተረጋግጧል ። ግን ሰዎቹን መመለስ አይቻልም።ይህ ደግሞ እነዚህ ሰዎች ምን ያህል ሊሳሳቱ እንደሚችሉ አጉልቶ ያሳያል ።

ናፖሊዮን ገና ዕድሜው 20 ዓመት ሳይሞላው ለፈፀመው ወንጀል በሞት እንዲቀጣ የተወሰነበት ነበር።ይህ ፍርድ ተፈፅሞበታል ። ይህንን ታሪክ ለቤተሰቦቹ ላካፍል እፈልጋለሁ ። እዚህ እስር ቤት ውስጥ ሆኜ ባገኘሁት አድራሻ ይህንን ደግነቱን ቤተሰቦቹ እንዲያውቁት ሞክሬአለሁ ። በሕግ ፊት ምንም እንኳ የሰው ሕይወት ያጠፋ ቢሆንም በዚች ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ደግነት የተሞላ ጥሩ ሰው እንደነበር ሊያውቁት ይገባል ። በመጥፎ ብቻ ሳይሆን በደግ ሥራው የምንደሰት እንዳለን ሊረዱት ያስፈልጋል ።

በሰላም ክረምልኝ .

ሊውስ

. . . . . .ይህንን ደብዳቤ አጥፌ ወደ ቦታው መለስኩና እንደ ገና ወደ ሃሳቤ ተመለስኩ ። በዛች በሶደሬ ክፍል እስር ቤት ውስጥ የነበረን ፍቅር ታሰበኝ ። በተለይ ገና እንደገባን የተደረገልንን አቀባበል አስታወስኩ ። የጆሆቫ ኃይማኖት ተከታዮች መጽሐፍ ቅዱስ ለማስተማር ሲጥሩ ፣ እኛ ማርክሲዝምን እንዲማሩ ስንታገል ፣ ከበርቴው ልደታን እንደለመኑ ቀኑ ይነጋል ይመሻል ። ከርከራችን ያተኮረው ጆሆቫዎቹ “ ሞት ለኢሕአፓ “ ብለው መፈክር አሰምተው እንዲፈቱ ለማሳመን ከልባችን እንጥር ነበር ። ሞት ለኛ ተመኝተው እነርሱ ሕይወት ቢያገኙ እንመርጥ ነበር ።“እናንተ አላችሁም አላላችሁም እኛ አንሞትምና በሉ“ ብለን እንለምናቸው ነበር ። ከኛ ጋር እንዲዘምሩ እንጠይቃቸዋለንም ። ግን አክርረው በኃይማኖታቸው ጠኑ ። አሁን ሳስበው የዛን ጊዜ ከእስር ቤት ውጭ ጆሆቫዎችን ባገኛቸው ኖሮ የኢምፔሪያሊዝም ኃይማኖት ብዬ አበሻቅጣቸው እንደ ነበር አልጠራጠርም። የሰው ልጅ የፈለገውን ሃይማኖት መከተል መብቱ መሆኑን የምናምን

ስንቶቻችን ነን ? ያን ያህል ደግነት፣ ያን ያህል ፍቅር ለኛ በዓላማ ለማንገናኝ ሰዎች እንደነበራቸው በአሁኑ ጊዜ ስመሰክርላቸው ደስታ ይሰማኛል።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሁኔታው እየከረረ መጣ ። እስሩ ተለወጠ ። በተለይ በጀሆቫዎቹ፣ በከበርቴው ነጋዴና ከከርቸሌ በመጣነው ላይ ነገሩ ከረረ ። ግቢው የጭንቀት ደመና አንዣበበት። በቅርብ አንድ አዲስ ክስተት እንደሚኖር የአብዮት ጥበቃዎቹ ሁኔታ ያስረዳል ። እነከሰተ ሞት የተፈረደባቸውን ላለማየት ነው መሰለኝ የሶደሬ እስር ቤት ክፍል ጉብኝታቸውን አቆሙ ። ሁኔታቸው ሁሉ ያጠራጥር ጀመር። የሃዘን ስሜት ግቢውን ሞላው። ወቅቱ ያሳዝናል ፣ ትካዜ ይከታል፣ አይ ጊዜ . . . . . . . . የዛሬውን ይመስል ነበር . . . . . .

መስኮቱ ላይ ቆሜ አሮጊቶች አብረው ቆመው ሲያወሩ ይታየኛል ። በዛን ጊዜ የታሰርን ልጆች ወላጆች እንደነዚህ አርጅተው ይሆን ? ብዙዎቹ ግን በሃዘን ሲቃጠሉኑረው ሞተዋል ። እነዚህም አሮጊቶች በሁለተኛው ዓለም ጦርነት ጊዜ የሚያሳዝን ታሪክ አጋጥሟቸው ይሆን ብዬ አሰብኩ። ግን አሁን ጡረታቸው ተከብሮ በደስታ ይኖራሉ ። በኛ አገር ግን ልጆች ለወላጆቻቸው መጦሪያ ነበሩ።የኛ ሃገር አሮጊቶችና ሽማግሌዎች የልጅ ፍቅር ብቻ ሳይሆን የሽምግልና ወቅት ጡረታቸውን ጊዜ ሥልጣን የሰጣቸው አረመኔዎች ሰረቋቸው። ልጆቻችውን በመግደል ካለ ጡረታ አስቀሯቸው። የመከራና የሥቃይ ኑሮ ውስጥ ኖረው ከዚህ ዓለም በድህነት በሃዘን ተቆራምደው ተለዩ።ኮምፒተሩ አሁንም ይጮኻል።ለፍላፊዋ ሴት እየደጋገመች “ ሞት ለኢሕአፓ “ ትላለች ። አሁን ኢሕአፓን መግደል ትችል ይሆን ? ብዬ እራሴን ጠይቄ ፈገግ አልኩኝ ። ደርግም ሞክሮ ሁሉንም ማጥፋት አልቻለም ። የሞቱት ልጆች ወላጆች አሁን ይህንን ቢሰሙ ምን ይሉ ይሆን ? አካላቸው የጎደለስ ? ሴትየዋ አዋቂ መባል ስለምትፈልግ ትጮኻለች እንጂ የስንት ሰው ቁስል በመቀስቀስ ላይ እንዳለች አይገባትም . . . . . . . .

. . . . . . . .የዛሬ አራት ዓመት ጥቅምት 20 . 2005 . . . . . . . ቴክሳስ ውስጥ ሊውስ የሞት ቅጣቱ ተፈፀመበት ። ዛሬ አራተኛ ዓመቱ ነው ። በዚህ ዓለም በግፍ ለተገደሉ ሁሉ በዚህ ቀን ሻማ ለማብራትና ለማስታወስ ወስኛለሁ ። ከዚህ ሃዘን ከሚቀሰቅስ ቀን ጋር የሃዘን ትዝታዬ ሁሉ አንድ ላይ መጥተው መንፈሴን ቢያስጨንቁት ፣ ታሪካቸውን ተናግሬ ይወጣልኝ እንደሆን ብዬ ይህንን ፅሁፍ ጀመርኩ ።

. . . . . . .የቴክሳሱ የእስር ቤት ጓደኛዬ ሊዊስ የመጨረሻ ቀኖች ታወሱኝ ። ምንም እንኳ በዚያ ቀን እንደሚገደል ባውቅም ከመሞቱ በፊት የመጨረሻው ደብዳቤው ሲደርሰኝ ምርር ብዬ አለቀስኩ ። የሊውስ ጭንቀት ታሰበኝ።ይህ ሰው በዚህ ወቅት የሚሰማው እኛ በሶደሬ የእስር ክፍል ውስጥ የተሰማንን ዓይነት ነው ። ልዩነቱ እሱ በርግጥ እንደሚገደል ያውቃል እኛ ግን በጥርጣሬ ብቻ ተሳቀን ነበር የከረምነው። በእያንዳንዱ አብዮት ጥበቃ ዓይን ላይ መልሱ ያለ ይመስል ከዓይኑ ለማንበብ የምናደርግ የነበረው ጥረት ማንም ሰው እንደገና እንዲገጥመው አልመኝም ። መሞት አንድ ቀላል ነገር ነው ። ነገር ግን ሞትን እየጠበቁ መኖር ምንግዜም ቢሆን ረጅምና አስቃቂ ነው ።

. . . . . .ትዝ ይለኛል የሚገደልበት ቀን ሲደርስ ልቤ እየደነገጠ መጣ፣እንቅልፍ እንቢ አለኝ ። ሃዘን ገባኝ ። ፎቶውን አውጥቼ አየሁት ። ያሳዝናል ። ለምን ተዋወቅሁት ? የሰው ነፍስ በማጥፋት ተባባሪ ሆነሃል በመባል ነው ("guilty by association")ተብሎ ነው የሞት ፍርድ የተፈረደበት እንጂ ወንጀሉን እንዳልፈፀመ የታወቀ ነው ።የቴክሰስ ሕግ “ገዳይም ተባባሪም በሞት ሊቀጡ ይችላሉ“ ይላል። ገንዘብ ያለው ፣ ሃብታም የሆነ ፣ አሜሪካ ውስጥ ጥሩ ጠበቃ ቀጥሮ እንደሚድን የታወቀ ነው ። ሊውስ ግን ገንዘብ የለውም ፣ የሚረዳው የለውም ፣ ደሃ በመሆኑ ሊገደል ነው ።የሰው ልጅ የሚሞትበትን ቀን ቢያውቀው ኖሮ ዓለም ምን ትመስል ነበር ? . . . .

በሰሜን አሜሪካ ሞት የተፈረደባቸው የመጨረሻ ራትና የመጨረሻ ቃል ይፈቀድላቸዋል። ሊዊስ ሊሞት ሲል የሰጠውን የመጨረሻ ቃል አገኘሁት ።የመጨረሻ ቃል መስጠት ትፈልጋለህ ? ብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ፣

“አዎ እፈልጋለሁ ። እናንተ የምትወዱትን ሰው አልገደልኩባችሁም ወይም አላስገደልኩትም። ( ግድያውን ለማየት ለመጡት የሟች ቤተሰቦች ) ምን አልባት አንድ ቀን ገዳዩን እንደምታገኙት አልጠራጠርም ። ምኞቴ በማንና ለምን እንደተገደለ ብነግራችሁ ነበር ።ግን አላውቀውም ።

በጣም የምትወዱትን ሰው እንዳጣችሁ ይገባኛል ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የኔም ቤተሰቦችና ጓደኞች የሚወዱትን ያጣሉ ። እንደኔ የናንተም ሰው በግፍ እንደተገደለ ይገባኛል ። አልገደልኩትም ከመሞቱም ጋር ምንም ግንኙነት የለኝም ። እናንተን ቤተሰቦቼንና ጓደኞቼን በጣም እወዳችኋለሁ ። ምንም እንኳ ብሞት ለእናንተ ያለኝ ፍቅር አይሞትም ።አምላክ ነፍሴን ላንተ እሰጣለሁ። ሁላችሁንም አመሰግናለሁ“ ።

ለሞት የቀረቡ ሰዎች የመጨረሻ ቃል የማይረሳ ትዝታ ጥሎ ያልፋል። የሊውስ ሞትን ባሰብኩ ቁጥር አብሮኝ የሚታሰበኝ ሶደሬ የእስር ክፍል ነው ። ሶደሬ ውስጥ በሕይወቴ ለሞት በጣም የቀረብኩበት ወቅት ነበር። የነከሰተ የተለመደ ጉብኝት ማቆም ፣ የአብዮት ጥበቃዎቹ እኛን ማጎሳቆል ፣ የጥበቃው ብዛት ፣ የእስር ቤቱ ዝምታ ፣በቅርበ አንድ አዲስ ነገር እንደሚኖር ካሳበቀልን በኋላ እንቅልፍ እንቢ አለን ። አናወራም ፣ አንጫወትም ወይም አንተኛም ። ሁላችንም በሃሳብ ማዕበል እንናወጣለን ። አስበን፣ አስበን መልሱ በትንፋሽ የሚያወጣ ይመስል አንዳንዴ ብቻ በጣም የታመቀና የሚያቃጥል ትንፋሽ እንተነፍሳለን ። የጭንቀት ፣ የመከራ ፣ ትንፋሽ . . . . . . . . .

አንድ ቀን በከፍተኛው ውስጥ የሚገኙ የየቀበሌው ሊቀ መናብርት ተሰበሰቡ ። ይህ የመጨረሻው ጥሪ መሆኑ ገባን። በአሁኑ ጊዜ ከጊዜው ርዝመት የተናሳ የተሰበሰቡትን በሞላ አላስታውሳቸውም ግን ብዙ ነበሩ። እነዚህ ፋሽሽቶች የእግዜርን ያህል ሥልጣን ከደርግ ተሰጥቷቸው ሰው ይኑር ፣ ይሙት ብለው ለመወስን ይችሉ ነበር። በውስጣቸው በመጠጥ ኃይል የጠነበዙ ፣በአብዮት ፕሮፖጋንዳ የተሞሉ ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የጥላቻ ፈረስ የሚጋልብባቸው ሲሆኑ ከእንደነ ከሰተና ከእንደ ለማ ደረሰ ዓይነቶቹ የሚፈጽሙት አብዮታዊ ግዴታቸውን መሆኑን የተነገራቸውን በሚገባ ለመፈፀም የሚሯሯጡ ነበሩ ።

- ለማ ደረሰ የከፍተኛ 22 ቀበሌ 02 ሊቀመንበር የነበረ ሲሆን በአስተማሪነት ዝቅተኛ ኑሮ ይኖር የነበረ ነው ። ለማ የመኢሶን አባል ሲሆን በከፍተኛው ውስጥ ብዙ ወጣቶችን ያስገደለ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ከእስር ተፈቶ አዲስ አበባ ውስጥ ይገኛል ። ወጣቶቹን በመግደሉ የሚያምን ሲሆን አሁንም ከመግደል አልቆጠብም ባይ ነው ። ወደፊት በሰፊው የምፅፈው የተወዳጇ የሳባ ጣሰው ( ከስልሳ ሚኒስተሮች ውስጥ የተገደሉት የኮኔሬል ጣሰው ሞጆ ልጅ ፣ የፋንቱ ( በቀይ ሽብር የገደሉት መስሏቸው እናቱ ጠዋት እንዲያገኙት በራፍ ላይ ጥለውት ሲሄዱ ተንፏቆ ማድቤት ገብቶ ተደብቆ በኋላ እናቱ ፊት የተገደለው )፣ አገኘሁ አያሌውና አሁን ስማቸውን የማላስታውሳቸው ብዙ ወጣቶች ገዳይ ነው ።
- መቶ አለቃ ደስታ - የፖሊስ አባል ሲሆን የሰደድ አባል የነበረ የከፍተኛ 22 ሊቀመንበር ነው። ደካማ በመሆኑ ከሰተና ለማ የመኢሶን አባላት ከሱ የበለጠ ስልጣን ነበራቸው ። በመጨረሻ ግን ከቀይ ሽብር በኋላ እነከሰተ ፣ እነለማ ፣ እነ ኮማንደር ቴዲ ፣ እነ ሳሙዔል ፣ እነ ቢንያም ከአረመኔው ከደርግ ፅሕፈት የምርመራ ከፍል አላፊ ከሻንበል ብርሃኑ ጋር ሲታሰሩ መቶ አለቃ ደስታ ቦታውን ያዘ ።
- ይግረም - የአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ፖሊስ ወታደር የነበረና ከማንም የበለጠ አረመኔ የሆነ ሲሆን በጩቤ ጥፍር መንቀል የሚወድና የሚያዘወትር ነበር ። ይግረም ከተክለሃይማኖት ጀምሮ እስከ ድሮ አሮፕላን ማረፊያ ድረስ በተደረጉ የነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር የተሳተፈ ነው ።
- ሌሎቹን ሊቀመንበሮች አሁን ስማቸውን አላስታውሳቸውም ። ግን አንዳንዶቹ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ ውስጥ የተደላደለ ኑሯቸውን ተያይዘውታል።

እስከ ሌሊት ድረስ ስብሰባ ካደረጉ በኋላ ተበተኑ ። ከዚያ ቀን በኋላ ጥበቃው የባሰ ጠነከረ ። አንድ ቀን ሌሊት ሁላችንም ተቀሰቀስን ። ሁላችንም ስላልተኛን ቶሎ ተነስተን ተቀመጥን ። በመጀመሪያ ደሳለኝና ውብሸት ተጠሩ ፣ ከዛም ጆሆቫዎቹ ተጠሩ፣ ከዛም ከበርቴው ሰውዬ ተጠሩ ።ሁላችንም ቀይ ሽብሩ ሊካሄድ መሆኑ ገባን። ይህንን ወቅት

ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ አስታውሰዋለሁ ። በሁሉም ፊት ላይ የአየሁትን የሞት ስዕል ከአይኔ ምንግዜም ሊጠፋ አይችልም።

ደሳለኝና ውብሸት ሁላችንንም በርቱ ብለውን ወጡ ። ለቀረነው ጓዶቻቸው የማበረቻቻ ቃላቸውን ሰጥተው ሞትን በጀግንነት ሊጠጧት እየተጣደፉ ፣ የቁስለኞችን እግር እዳይረግጡ እየተጠነቀቁ ሄዱ ።ቀጥለው የተጠሩት ጆሆባዎቹ ነበሩ ። መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ይዘው ተነሱ ። ወደ አባታቸው ቤት እንደሚሄዱ በፈገግታ የመጨረሻዋን እስትንፋሻቸውን ለመተንፈስ በቆራጥነት ገሰገሱ ። በመጨረሻ የተጠሩት ምንም ያልጠበቁት "አድሃሪ" ተብለው የታሰሩት አዛውንት ነበሩ ። እግራቸው ከዳቸው ፣ መጮኽ አቃታቸው ፣ የልጆቻቸው ፊት መጥቶ ፊታቸው የተደቀነ ይመስል የልጃቸውን ስም ጠርተው ጫማቸውን እንዲሰጣቸው ጠየቁት ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ነበር ሁኔታው የገባቸው ። እስረኛውን አንድ ጊዜ ከተመለከቱ በኋላ ልጆቼን ለማን ጥዬ ልሂድ? ብለው ጠይቀው መልሱን ከትንሳዔና ከከሰተ የሚያገኙት ይመስል እየተጣደፉ ወጡ ።

ከውጭ ድምፃቸው ይሰማናል ።ሁላችንንም ዓይናችን በእንባ ተሞላ ።ወደ ውጭ አውጥተው እጆቻቸውን አሰሯቸው ። አሁንም ይጮሃሉ።

"እረ ልጆቼን ለማን ጥዬ"ብለው በልመና ድምጽ ይጮኻሉ ።

" ትንሰዔ ምን አደረግሁ ?" . . . . . ልጆቼ ማን አላቸው ? . . . .እባከሽ የዛሬን ተይኝ . . . .ሁለተኛ ያልሽኝን ሁሉ እሺ እላለሁ. . . . . . ንብረቴን ሁሉ ውረሱት . . . ከባዶ እጀምራለሁ . . . . . እግርሽ ላይ ወድቄ ልለምንሽ . . . . ልጆች የሉሽም? . . . . ከሰተ እስቲ አንተ ተለመነኝ፤ . . . . ከነገ ዛሬ ትፈቱኛላችሁ ብዬ ስጠብቅ ?. . . .፣ እረ ባካችሁ በልደታ ! . . . እረ ባካችሁ በልጆቻችሁ . . . . ስለ ወንድ ልጅ አምላክ ! . . . . ግረፉና ሃብቴን ሁሉ ወስዳችሁ ተውኝ . . . . . "

መሪር የሲቃ ጩኸት ደግሞ በመሃል ያሰማሉ ፣

"ትንሳዔ ሴት አደለሽም ? . . . . ልጆች የሚሸከመው ማሕፀንሽ አይለመንም ? . . . . . ." ወደ ሌሎቹ የከበቡዋቸውን አብዮት ጥበቃዎች እየተማጠኑ "ደግሞ እባካችሁ እስቲ እንናተ ለምኑልኝ . . . . ሽማግሌ ሆኑኝ . . . . . ለልጆቼ እንጂ ለእኔ ሞትም ፣ ድህነትም ፣ መከራም ፣ ስቃይም አዲስ አደለም . . . . ጎበዝ ! . . . . የሃገር ወንድ ሁሉ ስሙኝ እንጂ ! . . . . . አልገደልኩ . . . . . ደም አልተቃባሁ . . . . . ለምን ይኸ ሁሉ? . . . . . ." ለጥያቄ መልስ ሲያጡ ደግሞ . . . . "እረባካችሁ አንድ በሉ? . . . . . ጨነቀኝ እኮ ዝም አትበሉ ?. . . . . ዝምታው ምንድነው? . . . . "

ከትንሽ ጊዜ በኋላ የትንሳዔ ድምፅ አንባሮቁ ልመናቸውን ገታው ። " ዝም በል አትለፍልፍ . . . . . አብዮቱ አንተን የመሰለ አድሃሪ አይፈልግም ! . . . . . . . አይፈልግህም. . . . " የሚያሰቅቅ የፌዝ ሳቋን በቀጭኑ ለቀቀችው ። "ትሞታለህ . . . . ትሞትታታለህ . . . . " አለች ደጋግማ ።

ድምፃቸው ተስፋ ባጣ ሁኔታ ተሰበረ። "እሺ እንግዲህ ልጆቼን ለማንም አደራ አልልም . . . . . ላንቺ ነው አደራ የምልሽ . . . . አደራ የምለው ማንም የለኝም . . . .በምድር የሰጠሁሽን በሰማይ እቀበልሻለሁ . . . . . የሴትነት ማሕፀንሽ በልጆች አልለመንም ካለ . . . . . ከለ ጥፋቴ ልትገይኝ ከፈለገሽ . . . . . የልጆቼን አደራ አንቺው ተቀበይኝ . . . . . እንደ ልጆችሽ አርገሽ አሳድጊልኝ . . . . . እንዳይርባቸው ፣ እንዳይጠማቸው አደራ . . . . . . " ። ድምፃቸው እየራቀ እየራቀ ሄደ ።ከግቢው መኪናዎች ተከታትለው ሲወጡ ይሰማናል ። ጥቂት ቆይቶ ከርቀት የጥይት ነጎድጓድ ሲወርድ ሰማን ። በሩቅ ።

በኋላ እንደሰማነው ብሪሞ ገደል ከዳገቱ ላይ አቁመው ወደ ገደሉ በጥይት እየመቱ ከተቷቸው ። አስከሬናቸውን ማንም እንዳያነሳው አብዮት ጥበቃዎች ሲጠብቁ

ውለው ከሰዓት በኋላ ተነሱ።ብሪሞ በደም የራሰ ምድር ሆነ ። ከብዙ ጊዜ በኋላ የጀሆቫዎቹን ፎቶ አገኘሁት ።



Faces we expect to see in the resurrection. All were murdered for their loyalty to the good news. From top left: Ayele Zelelew, Hailu Yemiru, Wubie Ayele, Kaba Ayana, Gebreyohanes Adhanom, Adera Teshome, Wondimu Demera, Kasa Gebremedhin, Eshetu Mindu

እንደነዚህ የመሰሉ ንፁህ ዜጎችን ጭምር ነበር የደርግ  ቀይ ሽብር ያጠፋው ። ከላይ የምትመለከቷቸው ሦስቱ ነበሩ በዚያ ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ የተገደሉት ።

ሴትዮዋ የምትጮኽበት ክፍል ውስጥ የተሰበሰቡት እነ ከሰተ ፣ እነ ለማ ፣ እነ ቴዎድሮስ ፣ እነ ሳሙዔል ፣ እነ ቢንያም ፣ እነ ደስታ ፣ ሊሆኑ ይችላሉ። ማን ያውቃል? እውነት በሠሩት ግፍ ተፀፅተው አሁን ሴትዮዋ በምትጮኽበት ክፍል ተሰብስበው የኑዛዜ ድምፃቸውን እንሰማ ይሆን ? እስቲ ሙያቸው ይመስክር ! ይህንን እያሰብኩኝ ኮምፒውተሩን አጥፍቼ ወደ ቤተክርስትያን ሄድኩ ።በግፍ ለተገደሉ ሁሉ ሻማ አበራሁ ። እኔ እዚህ ነኝ ልቤ ግን ከነሱ ጋር ነው  . . . . . . . . .  ብሪሞ አንድ ቀን በእነርሱ ስም ይሰየም ይሆን ?

## <u>እስከ ማዕዜኑ</u>

እስከ ማዕዜኑ አነብር ውስተ ልብየ ትካዘ
ዐሊውየ ሕገ ወትዕዛዘ ማርያም ኩነኒ መናዝዘ፣
ማርያም ኩነኒ መናዝዘ።

አቤል በፀጋ ርቆ ፣ በየዋህነት ከመጠቀበት ፣

ቃዬል በንፍገት ከብሮ ፣ መቀመቅ ከወረደበት ፣
የዕጓለመሕያው ታሪክ ፣ ሲጀምር የጠቆረበት
እንውረድ ብሎት ወንድሙን ፣ እስትንፋሱን የነጠቀበት ፣

ኃዘና ፣ ስምዒ ውበካያ ፣
ለሃገሪትነ ኢትዮጵያ ።

የሞት ታሪክ ሊዘከር
በአዝማናት ማህል ሊነገር
የመጀመሪያው መልአክ ፣ ታሪኩን ሲፅፈው እንደዚህ ነበር።
ከልዔቱ አኃው መንገደ ቀላይ ወረዱ፣
እነህ ሁለት ወንድሞች ወደ አዘቅት የሄዱ፣
አንደኛው ሚች ሊሆን ገዳይ ሊሆን አንዱ፣
አሃዱ ተመይጠ ወኢተመይጠ አሃዱ ፣
አንደኛው ሲመለስ ሁለተኛው እዚያው የቀረ፣
ውረድ እንውረድ ያለው ወንድሙ ገድሎት ነበረ።

ከዚህ የቀን ጎደሎ ነው ፣ ከዚህ ክህደት በኋላ፣
ከተራራው አናትና ከግርጌ በቆመው ማህል መተማመኑ የላላ።
የአዳም የልጅ ልጅ ሁሉ ምን ቢጀግን ምን ቢያቅራራ፣
ምን ደግ ንግርት ቢያስነግር ፣ ምን በማዕረግ ቢጠራ ፣
ይገሉኝ ይሆን እያለ ነው ፣ ውረድ ሲሉት የሚፈራ ።
እናም መውረድ ሞቱ ነው አንዴ ደርቡን ከወጣ ፣
ውረድ ሲባል በመውረዱ ነው ፣ ወንድሙ ሕይወቱን ያጣ።
በርግጥ ለምን ይወርዳል መውረድስ ለምን ጠቀመ ?
የወረደውን መግደሉ ለዘላለሙ ካልቆመ ! !

አበባው መላኩ - ደግ አይበረክትም ከሚለው የተገኘ

ሰለ ተሰውት የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !!!

Beljig.ali@gmail.com